ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ» (ሉቃ. 1÷31)፤ «ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ» (ማቴ. 1÷21)፤ «መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (የሐዋ. ሥራ 4÷12) የሚሉት ቃላተ መጻሕፍት በቂ ማስረጃዎች ናቸው።

## 5.1.6 ብሥራተ ገብርኤል መልአክ

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት የምሥጢረ ሥጋዌ መሠረት የሆነውን ብሥራተ መልአክ ለነገረ ማርያም ትምህርት መሠረት መሆኑን በስፋት አስተምረዋል። ስለሆነም መጋቤ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤል «ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ፤ ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ክብር ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ» (ሉቃ. 1÷28) ሲል ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን ያመሰገነበት ልዩ ምስጋና ከፍጡራን ሁሉ በላይ የሆነውን ንጽሕናዋንና ቅድስናዋን፣ ክብሯንና ልዕልናዋን በግልጥ ይመሰክራል። ይህም «ምልዕተ ጸጋ» የሚለው የመልአኩ ቃለ ውዳሴ በእመቤታችን ሕይወት ውስጥ ኃጢአትና ርኩሰት፣ በደልና መርገም አንዳችም ቦታ እንደሌላቸው ያስረዳል፣ ያስገነዝባል። ምክንያቱም ጸጋ እግዚአብሔር በምልዓት ባለበት ሕይወት ኃጢአትና ርኩሰት ሥፍራ የላቸውምና።[348]

ይህንን አስመልክቶ የብሕንሳው ሊቅ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ እመቤታችንን ባመሰገነበት ቅዳሴው «ኦ ድንግል አኮ ዘተአምሮ ርስሐተ ከመ አንስት እለ እምቅድሜኪ ወእምድኅሬኪ። አላ በቅድስና ወበንጽሕ ሥርጉት አንቲ፤ ድንግል ሆይ ከአንቺ አስቀድመው፣ ከአንቺም በኋላ እንደ ነበሩ ሴቶች እድፍ ጉድፍ የምታውቂ አይደለሽም። ይልቁንም በቅድስና፣ በንጽሕና ጸንተሽ ኖርሽ እንጂ»[349] ሲል ተናግሮላታል።

(348) እንዱዓለም ዳግማዊ (መምህር)፣ «እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል»፣ *ፍሬ ተዋሕዶ ዘእምናዝሬት*፣ ኅዳር 21/1997 ዓ.ም.፣ ገጽ 7።
(349) *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 120።



በወንጌል ቅዱስ ሉቃስ 1÷28 ላይ «ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ። ጌታ ካንቺ ጋር ነውና» ተብሎ በመልአክ እግዚአብሔር እንደበት የተነገረው ቃለ ብሥራት ጥልቅ የሆነ የምሥጢረ ድኅነት ትርጓሜ አለው። ይኸውም ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር የእመቤታችንን ባሕርይ በተዋሕዶ ፍጹም ባሕርዩ በማድረጉ ትስብእት የባሕርይ አምላክ እንደሚሆንና በዚህም መላው የሰው ዘር ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ ለመሆን በጸጋ መብቃታቸውን ያጠይቃል። ይህም በወንጌል ቅዱስ ማቴዎስ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ረቂቅና ድንቅ በሆነው የሥጋዌ ምሥጢር አማካይነት በረድኤት ያይደለ በኩነት ከእኛ ባሕርይ ጋር የመዋሐዱና አንድ የመሆኑ ምሥጢር በግልጽ ተነግሮአል።[350] (ማቴ. 1÷23፤ 28÷20) ስለሆነም በዚህ አማናዊ ምስክርነት መሠረት እመቤታችንን ምክንያተ ድኅነታችን አንቺ ነሽ እያልን ዘወትር እናከብራታለን፣ እናመሰግናታለን።

## 5.1.7 የቅድስት ኤልሳቤጥ ቃለ ውዳሴ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝታና ተመርታ የተናገረችውን የድንግል ማርያም ምስጋና ለነገረ ማርያም ትምህርቷ መሠረት፣ ለምስጋናዋ ደግሞ አብነት አድርጋ ትጠቀምበታለች። ስለሆነም ቅድስት ኤልሳቤጥ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ያቀረበችው ይህ ልዩ ምስጋና አስቀድሞ በመልአከ ብሥራት በቅዱስ ገብርኤል ከቀረበው ጣዕመ ውዳሴ ጋር ሌላ አዲስ ምሥጢራዊ ምስጋናም አለው። ይኸውም አዲስ ምስጋና «... ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ፤ ፍሬ ማኅፀንሽ የሆነው ጌታም የተባረከ ነው ማለት መርገመ ሥጋን፣ መርገመ ነፍስን የሚያርቅ፤ በረከተ ሥጋን፣ በረከተ ነፍስን የሚያድል ቡሩክ የባሕርይ አምላክ ነው» (ሉቃ. 1÷42)

(350) *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 70፣ 328። ቅዱስ ሳዊሮስ «ስለ ሃይማኖተ ኒቅያ»፣ *ሃይማኖተ አበው*፣ ገጽ 372። እንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፣ «እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል»፣ *ፍሬ ተዋሕዶ ዘእምናዝሬት*፣ ገጽ 7።
Laurentin, *The Hail Mary: Its Meaning and Its Origin*, 21.

የሚል ነው። ከዚህ ልዩ ቃለ ውዳሴም ከሣቴ ምሥጢር የሆነው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በመልአከ ሰላም በቅዱስ ገብርኤል ቃለ ብሥራት በተነገረው ምስጋና መሠረትነት የወላዲተ አምላክ የድንግል ማርያም ምስጋና በምልዓትና በስፋት፣ በጥልቀትና በርቀት እንዲታወቅና እንዲገለጥ ያደረገበትን ዐቢይ ምሥጢር እንረዳለን፣ እንገነዘባለን።

ከላይ የገለጥነው የቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም ውዳሴ የነገረ ድኅነት ምሥጢር ዐቢይ መሠረትና ቁልፍ ከሆነው የአምላክ እናትነት ጸጋዋና ክብሯ የመነጨና የተገኘ ልዩ ምስጋና ነው። ሌላው ምሥጢር ደግሞ ቅድስት ኤልሳቤጥ በመጽሔተ መንፈስ ቅዱስ አይታና ፍጹም ተረድታ እመቤታችን ድንግል ማርያምን «እሙ ለእግዚእየ፤ የጌታዬ እናቱ» ማለቷ መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ፣ ወልደ አምላክ የመሆኑን ምሥጢር በግልጽ መስክራለች። ከዚህ አማናዊ ምስክርነት ደግሞ ነገረ ማርያም ለነገረ ሥጋዌም ሆነ ለነገረ ድኅነት መሠረትና ምንጭ መሆኑን ይገነዘቧል። ምክንያቱም በመጀመሪያ እመቤታችንን እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ ናት ሳይሉ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክ ነው ብሎ ማመንና መቀበል አይቻልም። በአንጻሩ ደግሞ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ፣ ወልደ አምላክ ብለው ካላመኑ የምሥጢረ ድኅነት ተካፋይ ለመሆን ፈጽሞ አይቻልም። ስለሆነም በዘወትር ምስጋናችን ቅድስት ኤልሳቤጥን አብነት አድርገን ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያምን እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ እያልን የምንዘምርላት የድኅነታችን ምሥጢር የተከናወነባት መሠረተ ሕይወት፣ ምክንያተ ድኅነት በመሆኗ ነው።

ቅድስት ኤልሳቤጥ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን «ቡርክት አንቲ እምአንስት፤ እነሆ አንቺ ከሴቶች ሁሉ መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ ማለት መርገመ ሥጋ፣ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ ነሽ፤ በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን እያማለድሽ የምታሰጪ መዝገበ በረከት ነሽ» (ሉቃ. 1÷42) ብላ አመስግናታለች። ዳግመኛም «ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ»



በሚለው በዚህ አማናዊ ቃለ ውዳሴ መሠረት ቅድስት ድንግል እመቤታችን የሰው ልጆች ሁሉ ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ ክርስቶስን በትክክል የሚያውቁባትና የሚረዱባት መፌጺተ ልቡና፤ አምላካዊ ክብሩን የሚያዩባት መጽሔተ ምሥጢር፣ እንዲሁም ጸጋውንና በረከቱንም የሚያገኙባት መዝገበ በረከት መሆኗን ልብ ይሏል።

## 5.1.8 መራሒተ ፍኖት

ቅድስት ኤልሳቤጥ በመጽሔተ መንፈስ ቅዱስ አማካይነት በማኅፀነ ድንግል ማርያም የተቀረጸውን ረቂቅ አካላዊ ቃልን በማየቷና ይህንንም ታላቅና ድንቅ ምሥጢር ቃሏን አሰምታ በመመስከሯ ምክንያት እመቤታችን ወላዲተ አምላክ፣ መዝገበ ቃል፣ ዳግሚት አርያም ለመሆን መብቃቷን ይመለከቷል። ስለሆነም ቀደም ብለን በስፋት እንደገለጥነው ኦርቶዶክሳዊ የነገረ ማርያም አስተምህሮ የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት በአጽንኦት የሚመሰክረው የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት በሚገባ ለማወቅና ምሥጢሩንም ጠንቅቆ ለመረዳት ብሎም ለማመን መሠረት በመሆኑ ነው።[351] ይህንንም ዐቢይ ምሥጢረ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳውያን የቅዱሳት ሥዕላት ሊቃውንት [Orthodox Iconographers] *Hodegetria* ወይም «መራኂተ ፍኖት» ["She Who Shows the Way"] በተሰኘው የእመቤታችን ሥዕል አማካይነት ይገልጹታል። ይህ ኦርቶዶክሳዊ ሥዕል ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በቀኝ እጇ ወደ ልጇ ወደ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስታመለክት ያሳያል።

ከላይ የገለጥነው ኦርቶዶክሳዊ ሥዕል ምሥጢራዊ ትርጓሜው እመቤታችን ፍኖተ ሕይወት ዘበአማን (እውነተኛ የሕይወትና የጽድቅ፣ የድኅነት መንገድ) የሆነው ከእርሷ ባሕርይ የተገኘው (የተወለደው)

[351] Sheen, *The World's First Love*, 28-31. Laurentin, *The Hail Mary: Its Meaning and Its Origin*, 35 ,48-49. *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 68-71። አንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፣ «እነሆም+ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል»፣ *ፍሬ ተዋሕዶ ዘእምናዝሬት፣* ገጽ 7።



**ሥዕል 13፡- መራሒተ ፍኖት**

"ወሶበሂ ወለደቶ ዐቀበ ድንግልናሃ ዘእንበለ ርኩስ ከመ በጽንሳ ወንከር ትኩን መራሒተ ለሃይማኖት ዐባይ፤ በወለደችውም ጊዜ ድንግልናዋን ያስመለወጥ አጸና። ድንቅ በሚሆን ፅንሷ ለደገኛው ሃይማኖት መሪ ትሆን ዘንድ።"

(ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 240)

"በእንተ ተሠግዎቱ ለወልደ አምላክ እምኔኪ፤ ውብኪ ቀረባነ ኮነ እምድር ለማኅደር ውስተ አርያም። ብኪ ወበስመ ወልድኪ ቀረባነ ኮነ።"

(አንቀጸ ብርሃን፤ ገጽ 402)



አንድያ ልጇ መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን (ዮሐ. 14÷6፤ የሐዋ. ሥራ 4÷12) ለዓለም ማሳየቷንና ማስረዳቷን (ማስተዋወቋን) በመግለጥ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ወሳኝ ድርሻና መሠረታዊ አስተዋጽኦ በአጽንኦት ይመሰክራል።[352] ይህንን ታላቅና ድንቅ ምሥጢረ ድኅነት አስመልክቶ ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እመቤታችንን ባመሰገነበት በሰዓታት ድርሰቱ "ፍኖት ለኀበ አቡሁ አንቀጽ ዘመንገለ ወላዲሁ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ወደ ባሕርይ አባቱ ወደ እግዚአብሔር አብ የሚያደርስ የሕይወት መንገድ፣ ወደ አባቱም የሚያስገባ የጽድቅና የድኅነት በር እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው"[353] በማለት አስረግጦ ተናግሮአል።

## 5.1.9 የወንጌል ውዳሴ ማርያም

እንደሚታወቀው የወንጌለ ቅዱስ ሉቃስ መጀመሪያ ምዕራፍ ሁለት ዓይነት የብሥራተ መልአክ ታሪኮችን (ክስተቶችን) ይገልጻል። እነዚህም ብሥራተ ዘካርያስ ካህንና (ሉቃ. 1÷8-25) ብሥራተ ድንግል ማርያም (ሉቃ. 1÷26-38) ናቸው። ስለሆነም ቅዱስ ሉቃስ እንደጻፈው ወደ ካህኑ ዘካርያስም ወደ ቅድስት ድንግል እመቤታችንም የተላከው መልአክ ያው አንዱ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል መሆኑን ተናግሯል። ይሁን እንጂ መልአከ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ከወላዲተ አምላክ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ አስቀድሞ ከካህኑ ከዘካርያስ ጋር ካደረገው ንግግር በእጅጉ የተለየ ነው። ይኸውም ለዘካርያስ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ጸያሔ ፍኖት (የጌታ መንገድ ጠራጊ) የሚሆን ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅን እንደምትወልድ አበሠረው። ቤዛዊተ

(352) Heldman, *The Marian Icons of the Painter Fre Seyon: A Study in Fifteenth Century Ethiopian Art, Patronage, and Spirituality,* 117. Hainsworth, "The Ever-Virginity of the Mother of God," 16. Mascall, "The Mother of God," 173, 180-181, 191. Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God,* 47, 51, 55. Galot, *Mary in the Gospel,* 157-158.

(353) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 157።

ዓለም ድንግል ማርያምን ግን እግዚእ ዮሐንስ፣ አምላክ ዮሐንስ የሚሆን ጌታን እንደምትወልድ አበሠራት::

ሌላው ምሥጢር ደግሞ ካህኑ ዘካርያስ የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤልን ዜና ብሥራት በመጠራጠሩና ባለማመኑ ምክንያት አንደበቱ በመልአከ እግዚአብሔር ሥልጣን ተዘግቷል:: በአንጻሩ ደግሞ መልአኩ ወላዲተ አምላክን «እነሆም ትፀንሻለሽ እግዚአብሔር ወልድንም ትወልጃለሽ» ብሎ ባበሠራት ጊዜ «ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆንልኛል?» አለችው:: እርሱም መልሶ «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም» አላት:: በዚህን ጊዜ እመቤታችን ሲቁ «ዘንተ ትቤ ድንግል በእንተ ዘኢያርግ ውስተ ልባ ኅሊና እንበ እሙሕያው»(354) ብሎ እንደመሰከረላት የመልአኩን ቃል እንደ ዘካርያስ ሳትጠራጠር፣ እንደ ኒቆዲሞስ ሳትከራከር «እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ፣ ይደረግልኝ» ስትል በእምነት አረጋግጣ ተቀበለች:: በዚህም ምክንያት «ብፅዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገረኪ እምኀበ እግዚአብሔር፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ አግኝተው የነገሩሽ ቃል እንደሚፈጸም የምታምኚ አንቺ በእውነት ብፅዕት ነሽ፣ ንዕድ፣ ክብርት ነሽ» ተብላ ተመስግናለች::

ሌላው ደግሞ መጋቤ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ያመሰገነበት ምስጋና ከዚህ በፊት ከፍጡራን ወገን ለማንም ያልቀረበ፣ ወደፊትም የማይቀርብ ልዩ ምስጋና ነው:: ይህም ጣዕመ ውዳሴና ቃለ ፍሥሐ አስቀድሞ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት «ፈለግ ዘይውኅዝ ያስተፌሥሕ ሀገረ እግዚአብሔር፤ የወንዝ ፈሳሽ የእግዚአብሔርን ከተማ ፈጽሞ ደስ ያሰኛል ማለት ለጊዜው ሀገረ እግዚአብሔር የሆነች ኢየሩሳሌምን የዘሩባትን እንድታበቅል፣ የተከሉባትን እንድታጸድቅ ያደርጋታል» (መዝ. 45÷4) ሲል የተናገረው ቃለ ትንቢት ፍጻሜ ነው:: በመሆኑም የዚህ ቃለ ትንቢት ትርጓሜ ምሥጢሩ ዝናም ከላይ ከሰማይ እንዲወርድ ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ ከላይ ከሰማይ የወረደ

(354) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 200::*



መልአከ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል አማናዊት ሀገረ እግዚአብሔር ድንግል ማርያምን «ተፈሥሒ፤ ደስ ይበልሽ» ብሎ አንድም «ትጸንሲ ወትወልዲ፤ ትፀንሻለሽ እግዚአብሔር ወልድንም ትወልጃለች» ብሎ ደስ ያሰኛታል ማለት ነው:: (ሉቃ. 1÷26-28)

ዳግመኛም ኢየሩሳሌም ለእስራኤል ዘሥጋ የስንዴን ስብ በልተው የሚጠግቡባት፣ የወይን ጭማቂን ጠጥተው የሚረኩባት የበረከት ርስታቸው ናት:: በአንጻሩ ደግሞ መጽሐፍ «ኦ ማርያም ወላዲተ አምላክ ሀገር መንፈሳዊት ዘኃደረ ባቲ እግዚአብሔር ልዑል፤ አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም ሆይ ልዑል እግዚአብሔር ያደረብሽና የከተመብሽ ረቂቅ ከተማ ነሽ»(355) በማለት እንደመሰከረው አማናዊቷ ሀገረ እግዚአብሔር እመቤታችን ድንግል ማርያም እስራኤል ዘነፍስ የተሰኙ ምእመናን ሐዲስ የስንዴ ስብ የተባለ ኅብስተ ሕይወት ቅዱስ ሥጋውን በልተው የሚጠግቡባት፣ የወይን ጭማቂ የተባለ ማየ ሕይወት ደሙን ጠጥተው የሚረኩባት፤ በረከተ ሥጋን፣ በረከተ ነፍስን፣ የሚያገኙባት፣ በረድኤተ ሥጋ፣ በረድኤተ ነፍስ ተጠብቀው፣ ታፍረውና ተከብረው የሚኖሩባት አማናዊት የበረከት ርስታቸው ናት:: ሊቁ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ «... በኀበ ኵሉ መካን ርስት አንቲ፤ በቦታው ሁሉ አንቺ ርስት ነሽ»(356) እንዳለ::

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንም ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ «ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም ቅዱሳን መላእክት አይደሉምን?» (ዕብ. 1÷14፤ መዝ. 103÷4) ሲል እንዳስገነዘበው የድኅነተ ዓለምን የምሥራች ዜና ከልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ ምክንያተ ድኅነት፣ መሠረተ ሕይወት በሆነችው በድንግል ማርያም በኩል ለመላው ዓለም የሰበከውን፣ ክቡርና ገናና የሆነውን ይህን ባለውለታ መልአክ

(355) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ* 154:: Anthony, "Mary in the Orthodox Tradition," 96.
(356) *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 49-51::*

«ዐቢይ ውእቱ ክብር ዘተውህበ ለከ ኦ ገብርኤል መልአክ ዜናዊ ፍሡሐ ገጽ፡፡ ሰበከ ለነ ልደተ እግዚእ ዘመፅአ ኀቤነ፡፡ ወአብሠርካ ለማርያም ድንግል ዘእንበለ ርኵሰት፤ ደስ ያለህ ባለ ምሥራች መልአክ ገብርኤል ሆይ ላንተ የተሰጠህ ክብር ፍጹም ነው፡፡ ሰው ሆኖ ወደ እኛ የመጣ የጌታን ልደት በእመቤታችን በኩል ነገርከን፣ አስረዳኸን፡፡ ለድንግል ማርያምም አካላዊ ቃልን በድንግልና ፀንሳ፣ በድንግልና የመውለዷን ምሥጢር ነገርኻት»(357) እያለች ዘወትር ታከብረዋለች፣ ታመሰግነዋለች፡፡

ከላይ በዝርዝር የገለጥነውና በወንጌለ ቅዱስ ሉቃስ የተ መዘገበው የብሥራተ መልአክ ታሪክ በኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ዘወትር ለሚዘመረው የድንግል ማርያም ውዳሴ ዐቢይ መሠረትና ጉልህ ማስረጃም ነው፡፡ይህንን አስመልክቶ ፔሊካን ጃሮስላቭ የተባለው የሥነ መለኮት ምሁር [Pelikan Jaroslav] ሲናገር "ስለ እመቤታችን ስለ ድንግል ማርያም በሰፊው አብራርቶ የሚናገረው የቅዱስ መጽሐፍ ክፍለ ንባብ»(358) በማለት መስክሮአል፡፡ ስለሆነም በሰማያዊው መልአክ በቅዱስ ገብርኤል ቃለ ብሥራት የተገለጠው የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴ የማያቋርጥና እንደ ነቅዐ (ምንጭ) ሆኖ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ በሚነሡ ምእመናን አንደበትና ልቡና ሲቀዳና ሲፈስ የሚኖር ልዩ የምስጋና ጅረት ነው፡፡

ለዚህም በቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር የሚዘመረውና «በእንተዝ ንዌድሰኪ በከመ ገብርኤል መልአክ እንዘ ንብል ቡርክት አንቲ ማርያም ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ፡፡ ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ፤ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ሆይ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ፤ የማኅፀንሽ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስም የተባረከ ነው ብሎ እንዳመሰገነሽ እኛም ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ፣ ከነፍስሽ ነፍስን ነሥቶ በተዋሕዶ ፍጹም ሰው ሆኗልና ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ክብር፣ ምልዕተ ውዳሴ እመቤታችን ሆይ ደስ ይበልሽ

(357) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 100-101፡፡
(358) Jaroslav, *Mary Through the Centuries: Her Place in the History of Culture,* 16.



እያልን እናመሰግንሻለን»(359) የሚለው የድንግል ማርያም ምስጋና በቂ ማስረጃና ምስክርም ነው፡፡

በሞጋቤ ሐዲስ በቅዱስ ገብርኤል አማካይነት «ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ» ተብሎ ለአዲሲቷ ሔዋን ለድንግል ማርያም በቀረበው ልዩ ቃለ ውዳሴ መሠረት ወህቤ ሕይወት የሚሆን ጌታ ተገኝቷል፡፡ ይህ ደግሞ «በሕማም ለዲ፤ በምጥና በጭንቅ» የሚለውን ቃለ መርገም ሰምታ ምክንያተ ሞት የሆነውን ቃየልን ላስገኘች ለቀዳሚት ሔዋን ካሣ በመሆኑ ክብረ ቅድስት ድንግል ማርያም ከነገረ ድኅነት ጋር ያለውን ጥልቅ ግንኙነት በግልጥ ያስረዳል፣ ያስገነዝባል፡፡(360) ከዚህም ጋር የሥነ መለኮት ሊቃውንት መልአከ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል «መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ፤ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል» (ሉቃ. 1÷35) ሲል ለእመቤታችን ስለ ርደተ መንፈስ ቅዱስ የተናገረውን ኃይለ ቃል «የድንግል ማርያም በዓለ ኀምሳ» በማለት ገልጸውታል፡፡ ዳግመኛም በዕለተ ብሥራት የተገለጠው ይህ ልዩ ጸጋ ከትንሣኤ በኋላ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ለመቶ ሃያው ቤተሰብ እንደሚሰጥ የሚያመለክት በመሆኑ በዓለ ብሥራት «የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን» በመባል የሚታወቀውን በዓለ ኀምሳን በምሥጢር ያስተረጉማል፡፡(361) (የሐዋ. ሥራ 1÷8፤ 2÷1-12)

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እመቤታችን በወንጌለ ቅዱስ ሉቃስ የተናገረችውን የምስጋና ጸሎት «የድንግል ማርያም የምስጋና መዝሙር፣ የወላዲተ አምላክ መዝሙረ አኰቴት»(362) በማለት ይጠሩታል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውዳሴያትና ቅዳሴያት ሦስት

(359) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 166-167፡፡ ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት፣* ገጽ 38-40፡፡
(360) *ድርሳነ ገብርኤል፣* ገጽ 7-8፡፡ *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 166-167፡፡ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ አርጋኖን፣* ገጽ 228፡፡ *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው* ገጽ 328፡፡ St. Jacob of Serug, *On the Mother of God,* 30-32.
(361) Laurentin, *The Hail Mary: Its Meaning and Its Origin,* 36. አባ ጎርጎርዮስ፣ *የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣* ገጽ 26፡፡
(362) Laurentin, *The Hail Mary: Its Meaning and Its Origin,* 36. ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት፣* ገጽ 6፡፡

ዓይነት የአገላለጽ ዘይቤ አላቸው:: እነዚህም ቃለ ውዳሴ፣ ቃለ አንክሮና ቃለ አክብሮ ናቸው:: ስለሆነም በወንጌለ ቅዱስ ሉቃስ የተገለጸው ብሥራተ መልአክ ["Annunciation"]፣ እመቤታችን በቤተ ኤልሳቤጥ ያደረገችው ቆይታ ["Visitation"] እና ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም *["Magnificat"]* የቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም አስተምህሮ ምንጭና መሠረት ናቸው:: ከዚህም ጋር እነዚህ የምሥጢረ ሥጋዌ ጌጦች በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ለሚዘመሩት የእመቤታችን ውዳሴያትና መዝሙራትም መነሻና አብነትም ናቸው::(363)

በእነዚህ መነሻነትና መሠረትነት በየዘመናቱ የተነሡ ቅዱሳን አበው የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮ እንዲያድግና እንዲዳብር፣ በትምህርቱ ዘርፍ የነበረውም የዕውቀት አድማስ ስፋትና ጥልቀት እንዲያገኝ፣ ምሥጢሩም በትርጓሜ እንዲስፋፋና እንዲበለጽግ፣ ርቀትና ምጥቀት እንዲኖረው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: ይህ ደግሞ የቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያም ክብሯና ልዕልናዋ እንዲሁም ጣዕመ ውዳሴዋ ከነገረ ድኅነት ጋር በተገናዘበ መልኩ በስፋት እንዲቀናበር አስችሎአል:: በአጠቃላይ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት በሉቃስ 1÷26-45 ላይ በስፋት የተገለጠውንና ስለ እመቤታችን ሁለንተናዊ ዜና ሕይወት ማለትም ስለ ንጽሕናዋና ቅድስናዋ፣ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋ፣ ወላዲተ አምላክ መሆኗ፣ ለተዋሕዶ መመረጧና በድኅነተ ዓለም ጉዞ ውስጥ ስላላት ከፍተኛ ሚና የሚገልጸውን ክፍለ ንባብ **«የወንጌል ውዳሴ ማርያም»**(364) ይሉታል::

(363) Braaten and Jenson, *Mary, Mother of God,* 1-7. Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers,* 44. የሥነ መለኮት ምሁራን በቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር የሚጸለየውንና "ጸሎተ ማርያም" በመባል የሚታወቀውን የእመቤታችንን ምስጋና *Magnificat* ይሉታል:: የዚህ ስያሜ የት መጣው ከላቲን የተወሰደ ሲሆን ይህም የእንግሊዝኛው ንባብ "My soul *magnifies* the Lord" ብሎ ስለሚጀምር (ሉቃ. 1÷46-47) የላቲኑ ስያሜ ከተመሠረተበት የእንግሊዝኛው ቃል ጋር ተመሳሳይነት አለው:: Beima, "Hail Mary," 52.

(364) ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት*፣ ገጽ 5-6:: Russell, "The Blessed Virgin Mary in the Bible: The Scriptural Basis of Ecumenical Dialogue," 47.



## 5.1.10 የወንጌል መልክዐ ማርያም

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ በጉባኤ ሲያስተምር በጠለ ትምህርቱ የለመለመች፣ በጣዕመ ምሥጢሩ የረካችና የተመሰጠች አንዲት ሴት ከሕዝቡ መካከል ድምጿን ከፍ አድርጋ «ብፅዕት ከርሥ እንተ ፆረተከ ወብፁዓት አጥባት እለ ሐፀናከ፤ አንተን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን የተሸከመች ማኅፀን ብፅዕት ናት፤ የድንግልና ወተትን እያጠቡ ያሳደጉህ ጡቶችም ብፁዓን፣ ንዑዳን፣ ክቡራን ናቸው» (ሉቃ. 11÷27) ስትል በመድኃኒታችን አንጻር እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን አመስግናለች:: ዳግመኛም ቅዱሳን የእመቤታችንን አካሏንና ሕዋሳቷን የምልጃና የመማጸኛ መሣሪያ አድርገው ፈጣሪያቸውን ዘወትር የሚማጸኑበት በመሆኑ ይህ የቅዱስ ወንጌል ቃለ ውዳሴ **«የወንጌል መልክዐ ማርያም»** ተብሎ በምሥጢር ሊተረጎም ይችላል::

በመሆኑም ይህንን ቃለ ውዳሴ መሠረት በማድረግ የእመቤታችን የድንግል ማርያም ጣዕመ ፍቅሯና ጣዕመ ውዳሴዋ የበዛለት ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ ስለ እርሷ ክብር በተናገረበት የነገረ ማርያም የምሥጢር መድበል «ግዙፋኑን በሥጋ፣ ረቂቃኑን በመንፈስ አስተካክሎ የሚመግበውንና መጋቤ ፍጥረታት የሆነውን አምላክ በግዕዘ ሕፃናት ድንግልናዊ ወተትን የመገበች እርሷ በእውነት ብፅዕት፣ ንዕድ፣ ክብርት ናት»(365) ሲል ወላዲተ አምላክን አመስግኗታል:: ዳግመኛም ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ እመቤታችን ድንግል ማርያም እናትነትን ከድንግልና፣ ድንግልናን ከእናትነት አስተባብራና አንድ አድርጋ ይዛ የመገኘቷን ምሥጢር ሲያስረዳ «ድንግል ወለደት ፈጣሪሃ ወውእቱ ፈጠራ ኪያሃ፤ ድንግል ፈጣሪዋን በሥጋ ወለደችው፣ እርሱም እርሷን (እናቱን) ፈጠረ»(366) በማለት ድንግል ወእም (እናትም ድንግልም) የመሆኗን ምሥጢር አድንቋል::

(365) St. Jacob of Serug, *On the Mother of God,* 42.

(366) ቅዱስ ኤፍሬም፣ «በእንተ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም»፣ *ሃይማኖተ አበው*፣ ገጽ 150:: ተሾመ ዘሪሁን፣ (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት*፣ ገጽ 27-29::

ይህ የሊቁ ኃይለ ቃል አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በኋለኛው ዘመን ዓለምን ለማዳን (በሐዲስ ተፈጥሮ ለማደስና ለመቀደስ) ሰው በሆነ ጊዜ የፈጠረውን ሥጋ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በተዋሕዶ መንሣቱን አስረግጦ ይመሰክራል:: ዳግመኛም ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ "እንዘ ዓመቱ እሞ ፈለያ፤ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ቅድስት ድንግል ማርያምን አገልጋዩና ገረዱ ስትሆን ከቸርነቱና ከትሕትናው ብዛት የተነሣ እናቱ አደረጋት"(367) ሲል አስገንዝቦአል:: ከዚህም ኃይለ ቃል ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ከፍጡራን ወገን ስትሆን የፈጣሪዋ እናት ለመሆን መመረጧንና መታደሏን በዚህም እም ወአመት (እናትም አገልጋይም) መሆኗን ልብ ይሏል:: በአንጻሩ ደግሞ ይህ ልዩ ጸጋ ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በክብረ ወሊድ ላይ ክብረ ድንግልናን እንደተጎናጸፈች በምሥጢር ያስረዳል::

ቀደም ብለን እንደገለጽነው በሉቃስ 11÷27 ላይ "ብፅዕት ከርሥ እንተ ፆረተከ፤ ወብዕዓት አጥባት እለ ሐፀናከ"፤ ስፋሕና ረቂቅ፣ ምሉዕ በኵለሄ የሆንክ አንተን የወሰነችና ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን የተሸከመችህ ማኅፀን ብፅዕት ናት:: ዳግመኛም በዝናም አብቅለህ፣ በነፋስ ለይተህ፣ በፀሐይ አብስለህ ፍጥረትህን ሁሉ አስተካክለህ የምትመግብ አንተን ድንግልናዊ ወተትን አጥብተው ያሳደጉ ጡቶችም ንዑዳን፣ ክቡራን ናቸው ተብሎ የተነገረው አማናዊ ቃለ ውዳሴ "የወንጌል መልክዐ ማርያም" መሆኑን ተመልክተናል:: ምክንያቱም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስቲያኖች ዘንድ በስፋት የሚታወቀውና የሚጸለየው የመልክዐ ማርያም ድርሰት ማኅደረ መለኮት፣ መዝገበ ቃል፣ መቅደሰ እግዚአብሔር የሆነውን የድንግል ማርያምን ቅዱስ አካሏንና ሕዋሳቷን በማንሣትና በመዘርዘር ተገቢውን ምስጋና የሚያቀርብ ልዩ ጣዕመ ውዳሴ ነውና::

ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ "አንተን የተሸከመች ማኅፀን ብፅዕት ናት" የሚለውና በቅዱስ ወንጌል የተገለጸው የእመቤታችን ምስጋና

(367) ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 381፣ 389:: Brock, *Bride of Light*, 69. Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 59.



"ሰላም ለማኅፀንኪ ለእግዚአብሔር ማኅፈዱ፤ ዘሐነፀኪ የማነ እዴሁ፤ አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም ሆይ ንጹሐ ባሕርይ የሆነ ልዑል እግዚአብሔር በንጽሕና በቅድስና ለሸለመውና ላስጌጠው፣ ለቃሉ መዝገብነት፣ ለመለኮት ማደሪያነት ለመረጠውና ላከበረው ማኅፀንሽ ምስጋና ይገባል" ከሚለው የመልክዐ ማርያም ምስጋና ጋር በምሥጢር ይገናዘባል:: ዳግመኛም "ወብዑዓት አጥባት እለ ሐፀናከ፤ የጠባሃቸውም ጡቶች ብፁዓን፣ ንዑዳንና ክቡራን ናቸው" ተብሎ በቅዱስ ወንጌል የተመሰከረው ቃለ ውዳሴ "ሰላም ለአጥባትኪ እለ አውኃዛ ፍጹመ፤ ድንግልናዊ ሐሊበ ውስተ አፈ አምላክ ቅድመ፤ እመቤታችን ሆይ ሁሉን አስተካክሎ በሚመግበው ኃያል አምላክ ፊት የድንግልና ወተትን ላስገኙት ጡቶችሽ ክብር ይገባል" ከሚለው የመልክዐ ማርያም ቃለ ውዳሴ ጋር የተስማማ ነው::

የወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ሁለንተናዊ አካሏና ሕዋሳቷ ቅዱሳን ጻድቃን ምእመናን ዘወትር ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔርን የሚማጸኑባቸው የምልጃ ንዋያተ ቅድሳት ናቸው:: ይህንን አስመልክቶ "ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ" በመባል የሚታወቀው አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያምን ባመሰገነበት በሰዓታት ድርሰቱ:-

> ወይእዜኒ ንስእሎ ለመፍቀሬ ሰብእ እንዘ ንብል ተሣሃለነ እግዚኦ በእንተ ኵሉሙ ቅዱሳኒከ:: ... ወፈድፋደሰ በእንተ ማርያም እምከ እንተ ይእቲ ትምክህተ ዘመድነ:: በእንተ ማኅፀና ዘፆረከ፣ ወበእንተ ድንግልናሃ ዘኢረስሐ በጸኒሶትከ ወኢማሰነ በወሊዶትከ:: በእንተ አእዳዊሃ እለ ገሠሣከ፣ ወበእንተ አብራኪሃ እለ ሐቀፉከ፤ ወበእንተ አጥባቲሃ እለ ሐፀናከ፤ ወበእንተ ከናፍሪሃ እለ ሰዓማከ:: በእንተ ዘባና ዘሐዘለከ፤ ወበእንተ እእጋሪሃ እለ እንሶሰዋ ምስሌከ፤ በእንተ እዕዝንቲሃ ብፁዓት ወአእናፊሃ ምዑዛት፤ ወአዕዛኒሃ ሰማዕያት እለ ተበሥራ በቃለ ገብርኤል መልአክ:: ... በእንተ ብካያ ለእምከ:: በእንተ ኃዘና ለእምከ:: በእንተ ገዓሩ ለእምከ ...፤(368)

እያለ በዝርዝር ተናግሮአል::

(368) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ 130-133፣ 212-213፣ 245:: *መዝሙረ*

የዚህ ቃለ ተማኅፅኖ ምሥጢራዊ ትርጓሜ:- አሁንም ሰውን ወዳጅ የሆነ ጌታን ስለ ወዳጆችህ ስለ ቅዱሳንህ ሁሉ ብለህ ማረን፣ ይቅር በለን፤ እዘንልን፣ ራራልን እያልን እንለምነዋለን፣ እንማልደዋለን:: ... ይልቁንም ከቅዱሳኑ ሁሉ ይልቅ ማለትም ከሱራፌልና ከኪሩቤል፣ ከአእላፋት ወትእልፌተ አእላፋት መላእክት፣ ከነቢያት፣ ከሐዋርያትና ከወንጌላውያን፣ ከጻድቃንና ከሰማዕታት፣ ከካህናትና ከዲያቆናት፣ ከደናግልና ከመነኮሳት ሁሉ ይልቅ ሰውን የሚወድ ጌታን የባሕርያችን መመኪያ ስለሆነችው ስለ እናትህ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ብለህ ማረን፣ ይቅርም በለን፤ እዘንልን፣ ራራልን እያልን እንለምነዋለን፣ እንማፀነዋለን፣ እንማልደዋለንም::

ዳግመኛም ባሕረ ምሕረት ወደብረ ትዕግሥት የሆንክ ቸርና መሐሪ ይቅር ባይ አምላካችን ሆይ አንተን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ስለተሸከመህ ማኅፀኗ፣ ከእርሷ በመፀነስህ ምክንያት ስላልተለወጠውና በመወለድህም ስላልተሻረው ድንግልናዋ፣ ስለዳሰሱህ እጆቿ፣ ስለ ታቀፉህ ክንዶቿ፣ ስላሳደጉህ ጡቶቿ፣ ስለሳሙህ ከንፈሮቿ፣ ስላዘለህ ጀርባዋ፣ ካንተ ጋር ስለተመላለሱት እግሮቿ፣ ብሩሃት ስለሆኑት ዓይኖቿ፣ መዓዛ መለኮትህን ስላሸተተ አፍንጫዋ፣ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል አንደበት የምሥራች ዜናን ስለሰሙ ጆሮቿ ብለህ ይቅር በለን፣ ማረን፣ እዘንልን፣ ራራልን:: ... ስለ እናትህ ኃዘንና ልቅሶም ብለህ ይቅር በለን ማለት ነው:: በዚህም ቃለ ተማኅፅኖ መሠረት የወላዲተ አምላክ የድንግል ማርያም አካልና ሕዋሳቷ የምልጃ መገልገያዎች መሆናቸውን ይገነዘቧል::

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መሆኗን በአጽንኦት በመግለጥ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሱታፌ በስፋት የሚገልጸውና የሚመሰክረው ኦርቶዶክሳዊ የነገረ ማርያም

ድንግል፣ ገጽ 21-11:: Mascall, "The Mother of God," 261. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ አርጋኖን*፣ ገጽ 203-204:: አባ ጊዮርጊስ ሳግላዊ፣ [Abba Giyorgis Di Sagla]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር*፣ *["Il Libro Del Mistero"]*፣ ገጽ 2-3:: ቅዱስ ያሬድ፣ "አንቀጸ ብርሃን"፣ ገጽ 406::



አስተምህሮ ረቂቅና ጥልቅ የሆነውን የቤተ ክርስቲያናችንን የነገ ረ ሥጋዌ ትምህርትም በሚገባ ተንትኖ ያስረዳል:: ይኸውም ብሥራተ መልአክ ለምሥጢረ ልደት መቅድም ወይም መሠረት በመሆኑ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት በነገረ ድኅነት ትምህርታቸው ብሥራተ መልአክን "የምሥጢረ ሥጋዌ ዐቢይ በዓል"[369] ይሉታል:: በዚህም የቤተ ክርስቲያናችን ነገረ ማርያም እምነት የነገረ ሥጋዌ እምነቷን በሚገባ የሚገልጽና የሚያስረዳ መሆኑን ይመሰክቷል:: ስለሆነም ከላይ በገለጥነው ምሥጢራዊ ትርጓሜ መሠረት **ነገረ ማርያምና (Mariology) ነገረ ሥጋዌ (Christology) የማይለያዩና የማይነጣጠሉ የአንድ መጽሐፈ ሕይወት ሁለት ገጽታዎች ሲሆኑ ይህም ሕያው መጽሐፍ ነገረ ድኅነት (Soteriology) ነው::**

## 5.1.11 ኪዳነ ምሕረት (የምሕረት አማላጅ)

በኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ልዩ የክብር ሥፍራ የሚሰጣት በነገረ ድኅነት ውስጥ ታላቅ የሆነ ድርሻ ስላላት ነው:: ስለሆነም የክርስትና ሕይወት በምልጃ አገልግሎት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናንም እመቤታችን ባሕረ ምሕረት ወደብረ ትዕግሥት ከሆነው አምላክ የተሰጣትን የምሕረት ቃል ኪዳን ፍጹም በማመን በጸሎቷና በምልጃዋ ዘወትር ይማጸናሉ:: በዚህም መሠረት እናቱ ድንግል ማርያምን በዚህ ቃል ኪዳን ያከበረው አምላክ "ከመረጥኋቸው ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፤ ... ኪዳኔንም አላረክስም÷ ከከንፈሬም የወጣውን አልለውጥም" (መዝ 88÷3፣ 34) ሲል የገባውን አማናዊ ቃል ኪዳን ጠብቆ ዘወትር በይቅርታውና በምሕረቱ ይጐበኘናል፣ በቸርነቱና በረድኤቱም ይጠብቀናል::[370]

[369] Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God,* 19. Hainsworth, "The Ever-Virginity of the Mother of God," 5. McNamara, ed., *Mother of the Redeemer: Aspects of Doctrine and Devotion,* 153-155. ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት*፣ ገጽ 17::

[370] አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 158:: Malaty (Fr.), *St. Mary in the Orthodox Concept,* 61-62. Mascall, "The Mother of God," 171.

በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ ለምልጃ ሕይወት መሠረት የሆኑ ሁለት ዐበይት ነገሮች ሲሆኑ እነርሱም መንፈሳዊ ፍቅርና ትሕትና ናቸው። በመሆኑም መሐሪና ቸር የሆነው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ሲመላለስ ብዙዎች በፍጹም እምነት፣ ፍቅርና ትሕትና ሆነው ያቀረቡትን ልመና ተቀብሎ ተገቢውን መልስ እንደሰጠና የቸርነቱን ሥራም እንደሠራላቸው በቅዱስ ወንጌል በስፋት ተገልጿል። ከእነዚህም አያሌ ማስረጃዎች መካከል መድኃኒታችን በመዋዕለ ሥጋዌው ሲመላለስ በአልጋ ላይ ተኝቶ የነበረውን ሽባ ወደ እርሱ ይዘው ስለመጡት ሰዎች እምነት ሲል ማዳኑ (ማቴ. 9÷2)፤ የሮማዊውን መቶ አለቃ አገልጋይ በፊቱ ስለተላኩት የከበሩ የአይሁድ ሽማግሌዎች፣ ስለ መቶ አለቃው እምነትና ትሕትና ብሎ እንደፈወሰለት (ማቴ. 8÷5፤ ሉቃ. 7÷1-10)፣ እንዲሁም የከነናዊቷን ሴት ልባዊ ልመና አይቶና በቸርነቱ ተቀብሎ ልጇን እንዳዳነላት (ማር. 15÷21-28) በቅዱስ ወንጌል መገለጹ በቂ ማስረጃና ምስክር ነው።

ይልቁንም በማቴዎስ 15÷21-28 ላይ አምልኮተ እግዚአብሔርን ከማያውቁ አሕዛብ መካከል የሆነችና ኃጢአተኛ የነበረች አንዲት ከነናዊት ሴት ወደ መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርባ "ጌታ ሆይ የዳዊት ልጅ ማረኝ ልጄን ጋኔን ክፉኛ ይዞአታል ብላ ጮኸች።" ይህች ሴት ለልጅዋ አማላጅ ሆና ወደ ጌታችን ወደ ኢየሰሱ ክርስቶስ በመምጣቷ ልጅዋ ፈጽሞ እንደዳነችላት ተገልጿል። ታዲያ ከአሕዛብ ወገን በመሆኗ በጌታ አንደበት ውሻ የተባለችው ይህቺ ኃጢአተኛ ሴት ለልጇ አማላጅ ሆና ድኅነትን ካሰጠቻት፤ ሰማያዊው ንጉሥ እግዚአብሐር መዓዛ ንጽሕናዋን፣ መዓዛ ቅድስናዋንና መዓዛ ድንግልናዋን የወደደላት ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም የእናት አማላጅ አትሆነንም ይሆን? እርሷ እኮ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል አንበደት "... ደስ ይበልሽ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው። አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ ..." (ሉቃ. 1÷28) ተብላ



የተመሰገነችና እመቤት ናት። በመሆኑም ከላይ እንደገለጽነው አበው "የእናት አማላጅ ፊት አያስመልስ፣ አንገት አያስቀልስ" እንዲሉ ኦርቶዶክሳውያን መሠረተ ሕይወት፣ ምክንያተ ድኅነት በሆነችው በድንግል ማርያም አማላጅነት ፍጹም እናምናለን፣ እንታመናለን።

ዳግመኛም በዮሐንስ 19÷26-27 ላይ ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም የጌታ ወዳጅ ለሆነው ለቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ መንፈሳዊት እናት ሆና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የአደራ ቃል በቀራንዮ እግረ መስቀል እንደተሰጠችው ተመልክተናል። በመሠረቱ ቅዱስ ዮሐንስ በሥጋ የወለደችውና ያሳደገችው ሥጋዊ እናት እንደነበረችው በቅዱስ ወንጌል ተገልጿል። (ማቴ. 20÷20-24) ይሁን እንጂ እመቤታችን ለሐዋርያው ለቅዱስ ዮሐንስ የጸጋ እናት ሆና መሰጠቷ ከእግዚአብሔር ዘንድ ድኅነትንና ሕይወትን፣ ጸጋንና በረከትን ክብርን እያማለደች የምታሰጥና ልመናን የምታውቅ መንፈሳዊት እናት በመሆኗ ነው። (ሥዕል 7፣ 10፣ 14 ይመልከቱ)

## 5.1.12 ምዕራገ ጸሎት

እስትንፋሰ እግዚአብሔር የሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት በየገጻቸውና በየዓምዳቸው የቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ጉዞዋና ሁለንተናዊ አገልግሎቷ በቅዱሳን ጸሎትና ምልጃ አማካይነት ዘወትር ያማረና የሠመረ እንደሚሆን በስፋት ይገልጻል። (1ኛ ቆሮ. 15÷8፤ ኤፌ. 3÷7-13፤ ቈላ. 4÷2-4፤ የሐዋ. 1÷12-14) ኢትዮጵያዊው ሊቅ "ስዕለ ጸሎት ወስዕለ ትንባሌ እንበሌኪ ማርያም ዘያዓርግ ሱዓሌ፤ ድንግል ሆይ የሰው ልጆች ጸሎትና ልመና ውስተ ኑኀ ሰማይ የሚያርግብሽ ምዕራገ ጸሎት አንቺ ነሽ"[371] እንዳለ በኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ **የእመቤታችን የድንግል ማርያም አማላጅነት የቅዱሳን ሁሉ ጸሎትና ምልጃ አክሊል (ጉልላት) ነው።**

[371] አባ ጽጌ ድንግል፣ "ማኅሌተ ጽጌ"፣ ገጽ 613።

ዳግመኛም ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ እመቤታችንን ባመሰገነበት ውዳሴው "ሰኪ ጸጸሉ ዘእምኲሉሙ ቅዱሳን ትስእሲ ሰነ ኦ ምልዕተ ጸጋ፤ ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ክብር፣ ምልዕተ ውዳሴ ድንግል ሆይ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ትለምኝልን ዘንድ ላንቺ ይገባል"[372] በማለት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የመመኪያችን ዘውድ፣ የድኅነታችን መጀመሪያ፣ የንጽሕናችንም መሠረት ስለሆነች የእናት አማላጅ አድርገን ፈጣሪያችንን የምንማጸንባት የበረከት እመቤት መሆኗን ገልጾ መስክሮአል::

## 5.1.13 ደመና ኖኅ (የኖኅ ደመና)

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነገረ ማርያም ትምህርት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የምሕረት ዝናም የተገኘባት "ብርሃት ደመና ቀሊል" መሆኗን በመግለጥ የአማላጅነቷን ቃል ኪዳን በአጽንኦት ያስረዳል:: ይህንን አስመልክቶ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ ዘወትር የሚዘመረው የእመቤታችን ምስጋና "አንቲ ዘበአማን ደመና አንተ ስስተርእዪኪ ሰነ ማየ ዝናም:: ትእምርተ ዋሕዱ ፈሰየኪ ስብ፤ ድንግል ማርያም ሆይ ማየ ዝናምን ቋጥረሽ የታየሽልን እውነተኛ ደመና አንቺ ነሽ:: አንድም የኖኅ ደመና (ደመና ኖኅ) አንቺ ነሽ::"[373] ሲል የምልጃዋን አማናዊነት አስረግጦ ያስገነዝባል::

በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለጸው የይቅርታና የምሕረት ባለቤት የሆነው ልዑል ባሕርይ እግዚአብሔር ከማየ አይኅ (ከጥፋት ውኃ) በኋላ ለጻድቁ ኖኅ "እሠይም ቀስትየ በውስተ ደመናት ከመ ኢያማስና ለምድር ዳግመ በማየ አይኅ፤ እነሆ ምድርን ዳግመኛ በጥፋት ውኃ እንዳላጠፋት ከእናንተ

[372] *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 205:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 251-252:: Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 18, 39.

[373] *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 90፣ 99:: *መዝሙረ ድንግል*፣ ገጽ 34፣ 63:: ቅዱስ ያሬድ፣ *ዝማሬ መዋሥዕት*፣ ገጽ 125:: "ዘይነግሥ"፣ *መጽሐፈ ቅዳሴ*፣ (አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም.)፣ ገጽ 505-506:: O' Carroll, *Theotokos: A Theological Encyclopedia of the Blessed Virgin Mary,* 196. St. Jacob of the Serug, *On the Mother of God,* 70.



ጋር ለምገባው የምሕረት ቃል ኪዳኔ ምልክት ይሆን ዘንድ ቀስቴን በደመና አድርጌአለሁ" ሲል ተስፋውን ሰጥቶታል:: (ዘፍ. 9÷8-17) በዚህ አምላካዊ ቃል ኪዳን መሠረት የምሕረትና የይቅርታ ምልክት የሆነው ይህ የቃል ኪዳን ደመና በአራት ዓይነት ኅብር መገለጡ በኋለኛው ዘመን አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ አራቱን ባሕርያት (ባሕርያተ ሥጋ) ከአማናዊቷ ደመና ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ ለመንሣቱ ምሳሌ ነው::[374]

## 5.1.14 ደመና ኤልያስ (የኤልያስ ደመና)

ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ በዘመኑ በነበረው በንጉሡ አክዓብና በንግሥቲቱ ኤልዛቤል ጣዖት ማምለክ ተቆጥቶ፣ ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀንቶ ሰማይን ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ዝናም ለዘር፣ ጠል ለመከር እንዳይሰጥ በጸሎቱ ዘግቷል:: ይሁን እንጂ ከዘመነ አፀባ (ችግር) በኋላ ነቢዩ ኤልያስ በደብረ ቀርሜሎስ በጸለየ ጊዜ ከታላቅ ውቅያኖስ በተገኘች ታናሽ ደመና አማካይነት የምሕረት ዝናም እንደዘነበና ሕዝቡም በበረከት ጠግበው እንዳደሩ ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል:: (1ኛ ነገሥ. 17÷18፤ ያዕ. 5÷16-18) በዚህም መሠረት ማየ ሕይወት፣ ኅብስተ ሕይወት የሚሆን ጌታን ያስገኘች ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም አማናዊት ደመና ኤልያስ ትባላለች:: ከዚህም ጋር ልዑለ ቃል ኢሳይያስ "ወይወርድ እግዚእነ ውስተ ምድረ ግብፅ እንዘ ይጼዐን ዲበ ደመና ቀሊል፤ እነሆ÷ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ ወደ ግብፅ ይመጣል" (ኢሳ. 19÷1) ብሎ የተናገረላት አማናዊት ደመና መፍጠኒት (ፈጣን ደመና) እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት::[375]

[374] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ *ዕንዚራ ስብሐት ["The Lyre of Glory"] CSCO*፣ ገጽ 22:: Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia,* 4. Heldman, *The Marian Icons of the Painter Fre Seyon: A Study in Fifteenth Century Ethiopian Art, Patronage, and Spirituality,* 167, 196. ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት*፣ ገጽ 27-33:: አባ ጽጌ ድንግል፣ "ማኅሌተ ጽጌ"፣ ገጽ 595-596::

[375] *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 91-98::

ቅዱስ ኤፍሬም ከላይ በገለጥነው ቃለ ውዳሴ «ትእምርተ ዋሕዱ ረሰየኪ ስብእ እግዚአብሔር አብ በቀስትነት ሳለሽ፣ የዕርቅ ምልክት አደረገሽ» ብሏል:: ምሥጢራዊ ትርጉሙ ሰው ጠላቱን ባየ ጊዜ የቀስቱን አውታር ወደ ራሱ፣ ደጋኑን ደግሞ ወደ ጠላቱ ያደርጋል:: ይኸውም ትእምርተ ጸብ (የጸብና የክርክር ምልክት) ነው:: በአንጻሩ ደግሞ ሰው ወዳጁን ያየ እንደሆነ ደጋኑን ወደ ራሱ አድርጎ አውታሩን ወደ ወዳጁ ያደርጋል:: ይህ ደግሞ ትእምርተ ፍቅር (የፍቅርና የሰላም ምልክት) ነው::

ስለሆነም ዘፍቀደ ሰብእ የሆነው አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከአማናዊቷ ቀስተ ደመና ከድንግል ማርያም በተዋሕዶ የነሣው ሥጋ ከባሕርይ አባቱ ከአብ፣ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በክብር፣ በጌትነት፣ በምልዓት በመኖሩ ዘመነ ምሕረት ተሰብኳል፣ ታውጇል:: ይህም ይታወቅ ዘንድ የቀስተ ደመናው ደጋን ወደ ላይ ወደ ሰማይ፣ አውታሩ ደግሞ ወደ ታች ወደ ምድር ሆኖ ይታያልና ሊቁ እመቤታችንን በቀስትነት ሳለሽ የዕርቅ ምልክት አደረገሽ አላት::[376]

ሌላው ምሥጢር ደግሞ «እግዚአብሔር አብ የልጁ ምልክት አደረገሽ» ማለቱ ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከባሕርይው የወለደውን አንድያ ልጁን እመቤታችን ድኅረ ዓለም ያለ አባት እንድትወልደው ማድረጉን ሲያጠይቅ ነው:: ዳግመኛም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ወልደ እግዚአብሔርን ያለ አባት በሥጋ ስትወልደው ማኅተመ ድንግልናዋ አለመለወጡ፤ ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር ከእርሷ ሰው ሲሆን አምላክነቱ አለመለወጡን ያስረዳልና አብ የልጁ ምልክት አደረገሽ አለ:: በዚህም ድንቅ ምሥጢረ ተዋሕዶ እመቤታችን ድንግል ወእም (እናትም ድንግልም) መባሏ ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወሰብእ (ሰውም አምላክም) ሲባል ለመኖሩ ምሳሌ ነውና የልጁ ምልክት አደረገሽ አለ::[377]

[376] ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 99::
[377] ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 99::



## 5.1.15 አምስቱ የእመቤታችን ኃዘናት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት በመሆኗ በነገረ ድኅነት ውስጥ ባላት መጠነ ሰፊ ድርሻ ምክንያት ከሥላሴ ዘንድ የምሕረት ቃል ኪዳን ተሰጥቷታል:: እመቤታችን ባሕረ ምሕረት ከሆነው አምላክ ዘንድ በተቀበለችው በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት «ኪዳነ ምሕረት» ትባላለች:: በመሆኑም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ከልጇ ከወዳጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ የተሰጣት ልዩ የአማላጅነት ቃል ኪዳን በእርሱ ምክንያት በደረሰባት ጥልቅ ኃዘንና መከራ ላይ የተመሠረተ ነው:: ይኸውም አረጋዊው ስምዖን አስቀድሞ «በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል» (ሉቃ. 2÷35) ብሎ እንደተናገረው ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም መድኅነ ዓለም ክርስቶስ የሰውን ልጅ ለማዳን ወዶና ፈቅዶ ባደረገው አምላካዊ የቸርነት ጉዞ ውስጥ ያገኛትን መራራ ኃዘንና መጠነ ሰፊ መከራ አስመልክቶ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍት በስፋት ይገልጻሉ::

ይልቁንም ደግሞ የተአምሯ መጽሐፍ መጠነ ሰፊ ከሆነው የእመቤታችን መከራና ጥልቅ ኃዘኗ መካከል «አምስቱን ኃዘናት» በዋነኛነት ይገልጻል:: አምስቱ የእመቤታችን የድንግል ማርያም ኃዘናት የሚባሉትም:-

1ኛ. ስምዖን አረጋዊ[378] በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕማምና ሞት ምክንያት የኃዘን እናት እንደምትሆን በቤተ መቅደስ ትንቢት

[378] Galot, *Mary in the Gospel*, 85-90. McHugh, *The Mother of Jesus in the New Testament*, 104-112. Beima, "Hail Mary," 53. በቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ታሪክ እንደምንረዳው በንጉሡ በጥሊሞስ ዘመን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ከዕብራይስጥ ወደ ፅርዕ (ግሪክ) ቋንቋ ለመመለስ (ለመተርጎም) ሰብዓው ሊቃናት በተሰበሰቡ ጊዜ ለስምዖን አረጋዊ ትንቢተ ኢሳይያስ ደረሰው:: ስምዖንም መጽሐፈ ኢሳይያስን እየተረጎመ መጥቶ ከምዕራፍ 7 ቁጥር 14 ላይ ሲደርስ «እነሆ÷ ድንግል ትፀንሳለች÷ እግዚአብሔር ወልድንም ትወልዳለች÷ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» የሚለውን ዐቢይ ቃለ ትንቢት አገኘ:: በዚህን ጊዜ ከባድ ጥርጥር አደረበትና «እነሆ ድንግል ትፀንሳለች» የሚለውን ገጸ ንባብ ለውጦ «እነሆ ሴት ትፀንሳለች» ብሎ ጻፈ::

በተናገረ ጊዜ የተሰማት ጥልቅ ኃዘን፤ (ሉቃ. 2÷33-35)

2ኛ. ከኢየሩሳሌም ገቢረ በዓል ፍጻሜ በኋላ ልጇን ፈልጋ ባጣችው ጊዜ ያገኛት ኃዘን፤ (ሉቃ. 2÷41-47)

3ኛ. ሰማያዊው ንጉሥ ክርስቶስ እጆቹንና እግሮቹን ታስሮ በጲላጦስ አደባባይ መቆሙና መገረፉ፤ (ማቴ. 27÷1-2፤ ማር. 15÷1-2)

4ኛ. ማኅየዊ ጌታ በዕለተ ዓርብ የተቀበለው ሕማማተ መስቀልና በሁለት ወንበዴዎች መካከል በመስቀል ላይ መሰቀሉ፤ (ማቴ. 27÷38፤ ማር. 15÷27-28፤ ሉቃ. 23÷32-33)

5ኛ. መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ከመስቀለ መስቀል ወደ ታሕተ መቃብር መውረዱ ናቸው::[379] (ማቴ. 27÷57-60፤ ማር. 15÷42-47፤ ሉቃ. 23÷50-56፤ ዮሐ. 19÷28-42)

በመሆኑም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በዚህ ሁሉ አምላካዊ የድኅነተ ዓለም ጉዞ ውስጥ ተካፋይ መሆኗ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ከፍተኛ ድርሻና ልዩ ሥፍራ በግልጥ ያስረዳል፣

---

በመጨረሻም መልአከ እግዚአብሔር ተገለጠለትና ይህንን የነገረ ድኅነት ተስፋ ትንቢት ከዘመኑ ደርሶ ምሥጢራዊ ፍጻሜውን በዓይኑ ሳያይ እንደማይሞት በግልጽ ነገረው:: ይህም አማናዊ ተስፋ ጌታችን ከተወለደ በኋላ እመቤታችንና ዮሴፍ ሕፃኑን ኢየሱስ ክርስቶስን በአርባኛው ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ይዘውት በሄዱ ጊዜ መድኃኒታችንን ታቅፎ "ይእዜ ትስዕሮ ለገብርከ:: በሰላም እግዚኦ በከመ አዘዝከ:: እስመ ርእያ አዕይንትየ አድኅኖተከ፤ ጌታ ሆይ እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ:: ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና" (ሉቃ. 2÷29-31) ባለ ጊዜ ተፈጽሞለታል:: በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት ይህ በዓል "ልደተ ስምዖን" ይባላል:: በአንጻሩ ደግሞ የሥነ መለኮት ሊቃውንት ይህንን ታላቅ በዓል "የጌታ ወደ ቤተ መቅደስ መቅረብ" ["The Presentation of Christ in the Temple"] ይሉታል:: Baggley, *Festival Icons for the Christian Year*, 40-47. *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 338-340:: Brock, *The Bride of Light*, 78-79, 81-84, 158-189. O' Carroll, *Theotokos: A Theological Encyclopedia of the Blessed Virgin Mary*, 71, 387.

[379] ደቅስዮስ፣ "በእንተ ኃምስቱ ኃዘናት"፣ *ተአምረ ማርያም*፣ ገጽ 210:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 293:: *መዝሙረ ድንግል*፣ ገጽ 34፣ 63:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ አርጋኖን*፣ ገጽ 231:: Heldman, *The Marian Icons of the Painter Fre Seyon: A Study in Fifteenth Century Ethiopian Art, Patronage, and Spirituality*, 105.



ያስገነዝባልም:: ይህንን አስመልክቶ ሊቁ "ሰቆቃወ ድንግል አጽሐፍ በቀለመ አንብዕ ወአንጠብጥቦ፤ ወደሊ ወላህ ለደበለ ዘአንበቦ፤ የድንግልን መከራዋንና ስቃይዋን በእንባ ቀለም እጽፋለሁ:: ይህንን የድንግል እንባና መከራ ያነበበም ወዮ እያለ ፈጽሞ ይዘን"[380] ሲል በአጽንኦት መስክሮአል::

## 5.1.16 ርኅርኅተ ኅሊና

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌል "አባታችሁ ርኅሩኅ እንደሆነ እናንተም ርኅሩኆች ሁኑ" (ሉቃ. 6÷36) ብሎ እንደተናገረው መንፈሳዊት እናታችን የሆነችው ቅድስት ድንግል እመቤታችን ርኅርኅተ ልብ ናት:: ይህንን አስመልክቶ ሊቁ አባ ጽጌ ድንግል በማኅሌተ ጽጌ ድርሰቱ "እኮ ለሰብእ ባሕቲቱ ማርያም ሠናይት እመ ርኅርኅተ ልብ አንቲ ለኵሉ ፍጥረት፤ እመቤታችን ማርያም ሆይ ርኅራኄሽ ለሰው ልጅ ብቻ አይደለም:: ይልቁንም ለፍጥረት ሁሉ ርኅርኅተ ልቡና ነሽ"[381] ሲል ገልጾ ተናግሯል:: ዳግመኛም የተአምሯ መጽሐፍ ሲናገር ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ከርኅራኄዋ ብዛት የተነሣ ለተጠማ ውሻ ራርታና አዝና ውኃ እንዳጠጣች ይመሰክራል::

ይኸውም መጽሐፍ "ሰምዑኬ ኦ ፍቁራን ደቂቀ ወንጌል ብዝኀ ርኅራኄሃ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል በ፪ኤ ማርያም ወላዲተ አምላክ ከመ አስተዮት ማየ በአሣዕኒሃ ለጽሙእ ከልብ:: እመ ገብረት ዘመጠነዝ ርኅራኄ ላዕለ ከልብ እፎኑመ ትገብር ርኅራኄ ላዕለ ለዘይትአመኑ በትንብልናሃ፤ የተወደዳችሁ የወንጌል ልጆች ምእመናን ሆይ ለተጠማ ውሻ እንኳን ሳይቀር በጫማዋ ውኃ ያጠጣችውን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን የርኅራኄዋን ብዛት ስሙ:: እነሆ እመቤታችን ለተጠማ ውሻ ይህን ያህል ርኅራኄ ካደረገች፣ በጸሎቷና በአማላጅቷ ለሚያምኑና ለሚታመኑ፣ ይልቁንም ደግሞ በቃል ኪዳኗ ለሚማጸኑማ እንደምን አብዝታ ርኅራኄ አታደርግ?"[382] በማለት ያስገነዝባል::

---

[380] አባ ጽጌ ድንግል፣ "ሰቆቃወ ድንግል"፣ ገጽ 652::

[381] አባ ጽጌ ድንግል፣ "ማኅሌተ ጽጌ"፣ ገጽ 616::

[382] "ተአምረ ማርያም"፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 287:: *ተአምረ ማርያም*፣ ገጽ 275-276:: *መጽሐፈ ዕረፍት* *["The Book of the Dormition of St. Mary"]*, ed. Victor Arras,

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንም «የእናት ልመና ፊት አያስመልስ፣ አንገት አያስቀልስ» ነውና ይህንን የእመቤታችንን ብዝኃ ርኅራኄዋን በምእመናቿ ዘንድ በሰፊው በሚታወቀውና «ምስለ ፍቁር ወልዳ» በተሰኘው ሥነ ሥዕል አማካይነት ትገልጻለች:: በመሆኑም ድንግል ማርያምን ከልጇ ከወዳጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በአንድነት የሚያሳየው ይህ ኦርቶዶክሳዊ ሥዕል ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሰፊ ድርሻና መሠረታዊ ሚና በግልጥ ይመሰክራል:: ከዚህም ጋር በቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር በዘመነ ጽጌ የሚዘመረው የእመቤታችን ምስጋናም «ከመ ይትፌሣሕ ሕፃን ሶበ ይሬእዮ እሞ እትፌሣሕ አነሂ ሶበ ይሬእዮ ሥዕለኪ በርእየ ወተሳልሞ፤ ድንግል ማርያም ሆይ ሕፃን ልጅ እናቱን ባየ ጊዜ ፈጽሞ ደስ እንዲሰኝ፣ እኔም ሥዕልሽን በማየትና በመሳለም ደስ እሰኛለሁ»(383) በማለት ምሥጢሩን አጽንቷል::

## 5.1.17 ንጽሕት ዘር

ከዐበይት ነቢያት መካከል አንዱ የሆነው ልዑለ ቃል ኢሳይያስ ይህንን አማናዊ ምሥጢር ሲመሰክር «ወሶበ አኮ እግዚአብሔር ጸባዖት ዘአትረፈ ለነ ዘርዐ ከመ ሰዶም እምኮነ ወከመ ገሞራ እመሰልነ፤ የሠራዊት ጌታ አሸናፊ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር» (ኢሳ. 1÷9) ብሏል:: የዚህ ቃለ ትንቢት ትርጓሜ ምሥጢርም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በአዳምና በሔዋን ምክንያት ለመጣብን መርገምና ለተፈረደብን የሞት ፍርድ (ዘፍ. 3÷1-24)

Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium, vol. 342, *Scriptores Aethiopici*, t. 66 (text) (Louvain: Secretariat du Corpus SCO, 1973), 73-85. Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 9, 120-126.

(383) Heldman, *The Marian Icons of the Painter Fre Seyon: A Study in Fifteenth Century Ethiopian Art, Patronage, and Spirituality*, 176. Nouwen, *Behold the Beauty of the Lord: Praying with Icons*, 31-42. Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 63. *Patrologia Orientalis*, Tomus Primus vol. 1 eds., R. Graffin & F. Nau (Paris: Librairie de Paris, 1907), 648. አባ ጽጌ ድንግል፣ «ማኅሌተ ጽጌ»፣ ገጽ 641::



ቤዛ የሚሆን መድኃኒትን የምታስገኝ ንጽሕት ዘር ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን ባያስቀርልን ኖሮ ማለትም ከመርገመ ሥጋ፣ ከመርገመ ነፍስ አርቆ ለይቶ ከአንስተ ዓለም መርጦ ለተዋሕዶ ባያዘጋጅልን ኖሮ በኃጢአታቸውና በበደላቸው ምክንያት ኃያሉ አምላክ ተቆጥቶ በእሳትና በዲን እንዳቃጠላቸውና እንዳጠፋቸው እንደ ሰዶምና ገሞራ በሆንን ነበር ማለት ነው:: (ዘፍ. 19÷1-29፤ 2ኛ ጴጥ 2÷6-8) በመሆኑም ይህ ኃይለ ቃል ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ ለሰው ዘር ሁሉ ከዘላለም ሞትና ከማይጠፋው የእሳተ ገሃነም ኩነኔ መዳን ምክንያት የሆነችውን ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያምን በትንቢት መነጽር እያየት የተናገረው ተስፋ ትንቢት ነው::(384) ሊቁ «ከመ ሰዶም እምኮነ ወከመ ገሞራ እመሰልነ እግዚአብሔር ኪያኪ እመ ኢያትረፈ ለነ፤ ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም ሆይ እነሆ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር አንቺን ከአንስተ ዓለም መርጦ ለተዋሕዶ ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በጠፋን፣ ገሞራንም በመሰልን ነበር»(385) እንዳለ::

ስለሆነም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አስቀድሞ በቅዱሳን አበው ኅብረ አምሳልና በቅዱሳን ነቢያት ኅብረ ትንቢት፤ ኋላም በቅዱሳን ሐዋርያት ስብከትና በሊቃውንት ምሥጢራዊ ትርጓሜ በስፋት እንደተነገረው የድኅነታችን ምክንያት፣ የሕይወታችን መሠረት፣ በታመነው ቃል ኪዳኗ የምታማልደንና የምታስምረን የሰው ልጆች ሁሉ አለኝታና መመኪያ ናት:: ኦርቶዶክሳውያን ቅዱሳን አበውም እርሷን ባመሰገኑበት ድርሳናቸው ወላዲተ አምላክ በምሥጢረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሱታፌ ሲገልጡ «ሶበ ኪዳንኪ ምክንያተ ድኂን ኪሀሎ፤ ፈለገ እሳት ወደይን እምአስጠሞ ኵሎ፤ የድኅነት ምክንያት የሆነው የምሕረት ቃል ኪዳንሽ ባይኖር ኖሮ የእሳት ባሕር ሁሉን ባሰጠመ ነበር»(386) በማለት ምክንያተ ድኅነት፣ መሠረተ ሕይወት፣ ጥንተ መድኃኒት መሆኗን በግልጽ መስክረዋል:: ምክንያቱም ለእርሷ የተሰጠው

(384) *መጽሐፈ ትንቢተ ኢሳይያስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 9-10::*

(385) አባ ጽጌ ድንግል፣ «ማኅሌተ ጽጌ»፣ ገጽ 608::

(386) አባ ጽጌ ድንግል፣ «ማኅሌተ ጽጌ»፣ ገጽ 636::

የምሕረት ቃል ኪዳን ባይኖር ኖሮ የሰው ልጅ ሕይወት በድቅድቅ ጨለማ ኃጢአት ተውጦ፣ በሞት ጥላ ሥር ወድቆ፣ በመርገምና በሲኦል ቀንበር ታስሮ፣ በቀቢጸ ተስፋ ተይዞ ይቀር ነበርና ነው::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎትና ምልጃ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት የመጨረሻ ግብ ለመድረስ በእጅጉ እንደሚጠቅምና እንደሚረዳ ታምናለች፣ ታሳምና ለች፣ ታስተምራለች::(387) ቀደም ብለን እንደገለጥነው ኦርቶዶክሳዊ የነገረ ማርያም አስተምህሮ በወልደ እግዚአብሔር የቤዛነት ሥራ የተ ፈጸመው የሰው ልጆች ድኅነት (ሐዲስ ተፈጥሮ) በሦስቱ አካላት ማለትም በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድና ሥምረት የተከ ናወነ መሆኑን በግልጽ ይመሰክራል::

ከዚህም ጋር በዚህ አምላካዊ የማዳን ሥራ ውስጥ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ያላትን ልዩ ሱታፌ በጉልህ ያሳያል:: ምክንያቱም የድኅነተ ዓለም ጉዞ በምሥጢረ ሥጋዌ በኩል እንዲከናወን መሠረት የሆነችው እርሷ ናትና ነው:: ይህንን አስመልክቶ ዮሐንስ ሳዋርድ [John Saward] የተባለው ምሁር ሲገልጽ «በሥራተ መልአክ የምሥጢረ ሥጋዌ ዐቢይ በዓልና መሠረትም ነው»(388) ብሏል:: ስለሆነም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር የድኅነተ ዓለምን ሥራ ለማከናወን «እነሆኝ የጌታ አገልጋይ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ፣ ይደረግ ልኝ» (ሉቃ. 1÷37) የሚለውን የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ነጻ ፈቃድና ስምምነት መጠበቁ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ከፍተኛ ሚና ያረጋግጣል::

(387) አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 131-134:: Nouwen, *Behold the Beauty of the Lord*, 32.

(388) Saward, *Redeemer in the Womb*, 5. ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ጽጌ*፣ ገጽ 93፣ 170-171፣226፣388:: Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 200. McNamara ed., *Mother of the Redeemer: Aspects of Doctrine and Devotion*, 152-155. Nouwen, *Behold the Beauty of the Lord: Praying with Icons*, 34.



እንደሚታወቀው አበ ብዙኃን (የብዙዎች አባት) ተብሎ የሚጠራ ው የአብርሃም እምነትና ታዛዥነት ለብሉይ ኪዳን መመሥረት ምክንያ ት ሆኗል:: በአንጻሩ ደግሞ እመ ብዙኃን (የብዙዎች እናት) የተባለችው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ፍጹም ተአምኖና ተአዛ ዚነት ለአዲስ ኪዳን መጀመር መሠረት ጥሏል:: በዚህም ምክንያት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ብሥራተ መልአክን በቅድሚያ የሰማችና አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድን ከሁሉ በፊት አምና በፈቃዷ የተቀበለች በመሆኗ የሥነ መለኮት ሊቃውንት «የክርስቲ ያኖች (የአማንያን) ሁሉ መጀመሪያ (በኩር) ናት»(389) ይሏታል::

እመቤታችን ድንግል ማርያም በዚህ ፍጹም እምነቷና በነ ፈቃዷ ለነገረ ድኅነት አማናዊነት ያደረገችው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር በኃጢአቱና በበደሉ ምክንያት የወደቀውንና የተዋረደውን የሰው ዘር ፍለጋ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ወደዚህ ዓለም እንዲመጣ አድርጓል:: በአንጻሩ ደግሞ በዚህ የአካላዊ ቃል ርደት ምክንያት ዕርገተ ሥጋ (የሥጋ ክብር) መፈጸሙን ልብ ይሏል:: በወላዲተ አምላክ አማካይነት የተከናወነውን ይህንን ታላቅና ድንቅ ምሥጢረ ድኅነት አስመልክቶ በቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር የሚዘመ ረው የድንግል ማርያም ምስጋና «ኮንኪ ተንከተመ ለዕርገተ ውስተ ሰማይ፤ከምድር ወደ ሰማይ ለመውጣት ማለት ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከመርገም ወደ በረከት፣ ከኃጢአት ወደ ሥርየት እንዲሁም ከባርነት ወደ ልጅነት ለመሸጋገር የሕይወትና የድኅነት መሰላል ሆንሽ»(390) በማለት ተናግሮላታል::

(389) Carl E. Braaten and Robert W. Jenson eds., *Mary, Mother of God* (Grand Rapids, Michigan: William B. Eerdmans Publishing Company, 1996 ), 22. Payesko, *The Truth About Mary*, 1-xxi-1-xxii Biema, "Hail Mary," 50. Laurentin, *The Hail Mary: Its Meaning and Its Origin* ix-x, 35. Choan-Seng Song, *Third-Eye Theology* Revised Edition (Mary knoll, New York: Orbis Books, 1991), 149-152. St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 29.

(390) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 164-165::

ዳግመኛም ሊቁ ቅዱስ ያሬድ «... ከመ ትኩኒ ተንከተመ ለውሉደ ሰብእ ለሕይወት ዘለዓለም» ሲል መስክሮላታል። የዚህ ቃለ ውዳሴ ትርጓሜ ምሥጢሩም በመሰላል የላዩ ወደ ታች እንዲወርድበት ሰማያዊ መለኮት ከምድራዊ ትስብእት ጋራ ለመዋሐዱ፤ የታቹ ወደ ላይ እንዲወጣበት ምድራዊ ትስብእት ከሰማያዊ መለኮት ጋራ ለመዋሐዱና አንድ ለመሆኑ ምሥጢር አማናዊቷ ሰዋስው (የሕይወት መሰላል) ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም ምክንያት መሆኗን በግልጥ ያስረዳል፣ ያስገነዝባል።(391)

ዳግመኛም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ባላት ጉልህ ድርሻና ሰፊ አስተዋጽኦ ምክንያት ሰማይንና (እግዚአብሔርን፣ ቅዱሳን መላእክትን) ምድርን (ደቂቀ አዳምን) ያገናኘች የሕይወትና የጽድቅ መሰላል ናት። በዚህም ከብሉይ ወደ ሐዲስ፣ ከሕገ ርትዕ ኦሪት ወደ ሕገ ትሩፋት ወንጌል፣ ከመንፈሰ ረድኤት ወደ መንፈስ ልደት መሸጋገሪያ ድልድይ ሆናለች።

ከላይ እንደተመለከትነው እመቤታችን ድንግል ማርያም የጽድቅና የሕይወት መሰላል መባሏ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በሰፊው ለሚታወቀውና ለሚሠራበት የምልጃ ሕይወትና አገልግሎት መሠረት ነው። ይኸውም በመሰላሏ የታቹ ወደ ላይ እንዲወጣበት ጸሎታችንና ልመናችን፣ ጾማችንና ስግደታችን፣ ምጽዋታችንና ትሩፋታችን ሁሉ ወደ ሰማይ የሚወጣባትና የሚያርግባት ምዕራገ ጸሎት አማናዊቷ ተንከተም (መሰላል) ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ናት። ከዚህም ጋር በመሰላል የላዩ ወደታች እንዲወርድበት እመቤታችንም ዓስበ ጸሎታችንን፣ ዓስበ ጾማችንን፣ ዓስበ ስግደታችንን፣ ዓስበ ምጽዋታችንንና ዓስበ ትሩፋታችንን ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ

(391) ቅዱስ ያሬድ፣ «አንቀጸ ብርሃን»፣ ገጽ 410። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 212-213። *መጽሐፈ ዕረፍት* ["The Book of the Dormition of St. Mary"], ed. Victor Arras, *CSCO*, vol. 342, *Scriptores Aeithiopici*, t. 66 (text), 88-91. Graef, *Devotion to the Blessed Virgin*, 31-32.



የምናገኝባት በአማን ለእሊተ ምሕረት፣ ምዕራገ ጸሎት፣ አፍቅሮተ ረድኤት፣ አቁራሪተ መዓት፣ መዝገበ በረከት፣ መሠረተ ሕይወት የሆነችው አማናዊት ሰዋስው (መሰላል) ናት።

## 5.1.18 ማዕጠንተ ወርቅ

በኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት አስተምህሮ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሰማያውያን ካህናት (ሱራፌል) እጅ ውስጥ ባለች ማዕጠንተ ወርቅ ትመሰላለች። ይህም በዕለተ ዓርብ በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ አንጻር ለሰው ልጆች ሁሉ መንፈሳዊት እናት ሆና በጸጋ የተሰጠችበትን የአማላጅነቷን ምሥጢር ያጠይቃል፣ ያመለክታል። ይህንን አስመልክቶ ታላቁ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ እመቤታችንን ባመሰገነበት በአንቀጸ ብርሃን ድርሰቱ ሲናገር «ናስተማስለኪ ኦ እግዝእትነ በማዕጠንት ዘወርቅ ዘውስተ እደዊሆሙ ለሊቃነ ካህናት ሰማያውያን እለ ይከውኑ ጸሎተ ኩሎሙ ቅዱሳን ወሃይማኖቶሙ እምዲበ ምድር በውስተ ማዕጠንትሙ፤ ከማሁ በአስተ ለምኒ ያዐርጉ ስእለተሙ ለደቂቀ እጓለ እመሕያው ውስተ ማኅደረ ሥሉስ ቅዱስ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ እመቤታችን ሆይ በምድር ያሉ የቅዱሳን ጻድቃን ምእመናንን ጸሎትና ልመና ዘወትር ቅድመ እግዚአብሔር በሚያሳርጉ በሰማያውያን ካህናት (ሱራፌል) እጅ ውስጥ ባለች የወርቅ ማዕጠንት እንመስልሻለን። እንዲህም ስለሆነ ዘወትር በስምሽ አምነው፣ በአማላጅነትሽና በቃል ኪዳንሽ የሚማጸኑ የሰው ልጆችን ጸሎትና ልመና ልዩ ሦስት ወደሚሆኑ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ያደርሳሉ፣ ያሳርጋሉ»(392) ብሏል።

ከዚህም ጋር እመቤታችን የተመሰለችበት ማዕጠንት የወርቅ መሆኑ ምዕራገ ጸሎት የሆነችው ቤዛዊተ ዓለም ቅድስት ድንግል ማርያም በንጽሐ ሥጋ፣ በንጽሐ ነፍስ፣ በንጽሐ ልቡና የተሸለመችና ያጌጠች ንጽሕት በድንግልና፣ ሥርጉት በቅድስና፣ ክብርት በልዕልና መሆኗን ያጠይቃል።

(392) ቅዱስ ያሬድ፣ «አንቀጸ ብርሃን»፣ ገጽ 409። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 149-150።

ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖችም በዚህ ጽኑ እምነት ላይ ተመሥርተው እመቤታችንን ድንግል ማርያምን "ብሥራተ ገብርኤል መልአክ በከመ ሰማዕኪ ሰሚዐ ስምዐነ በአዕዛንኪ ሶበ ንጼሊ ማርያም ኀቤኪ፤ ምዕራገ ጸሎት ድንግል ማርያም ሆይ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤልን ዜና ብሥራት መስማትን እንደሰማሽ፤ እንዲሁም በስምሽ አምነን፣ በአማላጅነትሽ ተማጽነን በጸለይን ጊዜ ጸሎታችንን በእውነት ስሚን (አሳርጊልን)"(393) እያሉ ዘወትር ይማጸኑባታል:: ስለሆነም አበው "የሚያምኑትን ልኮ አይጠራጠሩም" እንዲሉ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም እሳተ መለኮትና ትስብእት የተዋሐዱባትና የተስማሙባት አማናዊት ማዕጠንተ ወርቅ በመሆኗ ጸሎታችንና ልመናችን ሁሉ ቅድመ እግዚአብሔር የሚደርስባትና የሚያርግባት አማናዊት ምዕራገ ጸሎት መሆኗን ፍጹም እናምናለን፣ እንታመናለን፣ እናሳምናለን::

## 5.1.19 መሠረተ ሕይወት ወምክንያተ ድኅነት

በቅዱሳት መጻሕፍት በስፋት እንደተገለጸው መፍቀሬ ሰብእ የሆነው ልዑል ባሕርይ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው አምላካዊ የድኅነት ዓላማና በጎ ፈቃድ እንዲፈጸም "የእግዚአብሔርና የሰዎች ፈቃድ ስምምነትና አንድነት" ["divine-human cooperation"] የግድ ያስፈልጋል:: የሥነ መለኮት ሊቃውንት ይህንን አምላካዊና ሰብአዊ የፈቃድ አንድነትና ስምምነት ሲነርጂያ *["Synergia"]* ይሉታል:: ይህም ኃይለ ቃል የጸጋ እግዚአብሔርና የሰው ልጆችን ነጻ ፈቃድ መስማማትና አንድ መሆንን የሚያመለክት ዐቢይ ምሥጢራዊ ቃል ነው:: በዚህ መሠረት ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የዚህ ታላቅ ምሥጢር ጉልላት (አክሊል) መሆኗን በአጽንኦት ይመሰክራሉ::(394) ይህንንም ቀደም ብለን በክፍል 2.1.1 ላይ

(393) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት፣* 230፣ 239:: Gambero, *Mary and the Fathers of the Church: The Blessed Virgin Mary in Patristic Thought,* 387-388.

(394) Jaroslav, *Mary Through the Centuries: Her Place in the History of Culture,* 4. Mascall, "The Mother of God," 171. Ware, *The Orthodox Church,* 221-222, 258-259.



በገለጥነውና የኦርቶዶክሳዊ ነገረ ማርያምና ነገረ ድኅነት አስተምህሮ መሠረት በሆነው በቀዳሚት ሔዋንና በዳግሚት (አዲሲቷ) ሔዋን በድንግል ማርያም መካከል ባለው ምሥጢራዊ ንጽጽር ይገነዘቧል::

በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሁለንተናዊ ሕይወት ውስጥ ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም ልዩ ሥፍራ የሚሰጣት ቀዳሚት ሔዋን ለሰው ልጆች ጥፋትና አስከፊ ሕይወት ተባባሪ ለሆነችበት ስሕተት ካሣ በመሆኗ ነው:: ይህንን አስመልክቶ ጥንታዊው የቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም መድበል ሲገልጽ:- "የምታዩት ይህ ዓለም በውስጡ የተደረጉ ሁለት ዓይኖች አሉት:: ቀዳሚት ሔዋን ጨለማ የዋጠው የግራው ዓይን ስትሆን፤ ዳግሚት ሔዋን እመቤታችን ድንግል ማርያም ደግሞ ብርሃን የታየባት የቀኙ ብርሀት ዓይን ናት" ["The world you see, has two eyes fixed in it: Eve was its left eye, blind, while the right eye, bright, is Mary."](395) በማለት አስረግጦ ተናግሮአል::

ከዚህም ሌላ በዜና አበው ሊቃውንት ዘንድ "የነገረ ማርያም አባት" ["The Father of Mariology"] በመባል የሚታወቀው ሊቁ ቅዱስ ሄሬኔዎስ [St. Irenaeus] በቀዳሚት ሔዋንና በዳግሚት ሔዋን በድንግል ማርያም መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ንጽጽር ከነገረ ድኅነት ጋር በማገናዘብ ሲያስረዳ:- "የቀዳሚት ሔዋን ያለመታዘዝ ቋጠሮ በዳግሚት ሔዋን በድንግል ማርያም ተአዛዚነት ተፈታ:: ይኸውም ድንግላዊት ሔዋን ባለማመኗ ምክንያት አጥብቃ ያሠረችውን ድንግል ማርያም ልዩ በሆነው ጸጋዋና ጽኑ በሆነው እምነቷ ፈታች" ["The Knot of Eve's disobedience was loosed by the obedience of Mary. For what the virgin Eve had bound fast through unbelief, this did the Virgin Mary set free through faith."](396) ሲል መስክሮአል:: ስለሆነም በቤተ

(395) Bride, *Bride of Light,* 32, 92-93.

(396) St. Irenaeus, "Adversus Hereses, Book III," *Ante-Nicene Fathers: The Apostolic Fathers, Justin Martyr, Irenaeus* vol. 1, 455.

ክርስቲያናችን የነገረ ድኅነት አስተምህሮ መሠረት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በመጋቤ ሐዲስ በቅዱስ ገብርኤል ቃለ ብሥራት አማካይነት ለቀረበላት አምላካዊ የድኅነት ጥሪ «ይኩንኒ በከመ ትቤለኒ» ብላ በፍጹም እምነት በጎ ፈቃዷን መግለጧ አምላካዊ የድኅነተ ዓለም እቅድ እንዲፈጸምና የሥጋዌ ምሥጢርም በእርሷ በኩል እንዲከናወን ማድ ረጉን እንመለከታለን:: (መጽ. ሲራክ 15÷14-16)

የቤተ ክርስቲያናችን መተርጉማን **«ወድቀው ይነሢል በእድ፤ ዘግይተው ይከብሯል በልድ»** ብለው እንደተናገሩት በሴት (ቀዳሚት ሔዋን) ምክንያት የመጣው ድቀተ ኃጢአትና መርገም በሴት (በዳግሚት ሔዋን በድንግል ማርያም) አማካይነት ተሽሯል፣ ተደምስሷል:: ይህም ማለት ቀዳሚት ሔዋን ለአዳም የሰጠችውና ያበላችው የዕፀ በለስ ፍሬ በመላው የሰው ዘር ላይ መርገምንና ሞትን አስከትሏል:: በአንጻሩ ደግሞ ዳግሚት ሔዋን እመቤታችን የሰጠችን ፍሬ ማኅፀኗ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍሬ ሕይወት፣ ፍሬ መድኃኒት፤ አንድም ዕፀ ሕይወት ወዕፀ መድኃኒት ሆነልን:: ዳግመኛም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ፍሬ ሕይወት የሆነ ጌታን ያፈራች ዕፅ፣ ማየ ሕይወት ጌታን ያስገኘች ዐዘቅት ኆትምት (የተዘጋችና የታተመች የውኃ ጉድጓድ) ስለሆነች ክብሯና ምስጋናዋም እንዲሁ ልዩ ነው::(397)

## 5.1.20 እመ ብዙኃን (መንፈሳዊት እናት)

ከላይ ከገለጥነው ምሥጢር ሌላ ቀዳሚት ሔዋን «እመ ሕያዋን፣ የሕያዋን ሁሉ እናት» (ዘፍ. 3÷20) ተብላ ትጠራበት የነበረውና በኋላ ግን ባለማመኗና ባለመታዘዟ ምክንያት ያጣችው የክብር ስሟና የእናትነት ማዕረጓ በዳግሚት (አዲሲቷ) ሔዋን በድንግል ማርያም አማካይነት መመለሱ እመቤታችን በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ወሳኝ ድርሻ ያሳያል:: ከዚህም ጋር የወላዲተ አምላክን የእናትነት ክብሯን

(397) Bettenson, *The Early Christian Fathers,* 126. Malaty (Fr.), *St. Mary in the Orthodox Concept*, 41, 49.



እንዲሁም የምስጋናዋን ታላቅነት በግልጽ ይመሰክራል:: ይኸውም የድኅነተ ዓለም ሥራ በቀራንዮ ተራራ በተፈጸመባት ዕለት ከእግረ መስቀል አጠገብ በነበረው ታማኝ ሐዋርያ በፍቁረ እግዚእ ቅዱስ ዮሐንስ አማካይነት ለዓለሙ ሁሉ እናት ሆና በጸጋ በመሰጠቷ ፍጻሜውን አግኝቷል:: (ዮሐ. 19÷26-27) በዚህም ምክንያተ ስሕተት ወሞት የሆነችውን የመጀመሪያ የሥጋ እናቱን ቀዳሚት ሔዋንን በዕፀ በለስ ምክንያት በማጣቱ አዝኖና ተክዞ ይኖር የነበረው መላው የሰው ዘር በምትኩ ምክንያተ ሕይወት ወበረከት የሆነችውን ዳግሚት ሔዋን ድንግል ማርያምን በዕፀ ሕይወት መስቀል አማካይነት በማግኘቱ ፈጽሞ መደሰቱን ይገነዘቧል::(398) (ሥዕል 6 ይመልከቱ)

በመሆኑም እመ ብዙኃን የሆነችው ቤዛዊተ ዓለም ቅድስት ድንግል ማርያም በዚህ የመንፈሳዊ እናትነት ጸጋዋ በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ወርቀ ደም ለተመሠረተችውና ለከበረችው ቤተ ክርስቲያን (ማኅበረ ምእመናን) የቃል ኪዳን እናት ["The nucleus of the New Church"] ለመሆን በቅታለች:: ፉልተን ሺን [Fulton Sheen] የተባለው ሊቅ የተሰጠው ይህ ታላቅና ድንቅ አምላካዊ ምሥጢር (በሐዲስ ተፈጥሮ) የተከናወነበትን ዕለት (ዕለተ ዓርብ) **«የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ መንፈሳዊ የልደት ቀን»**(399) በማለት ሰይሞታል:: ዳግመኛም በዚህ ድንቅ አገላለጽ መሠረት ዕለተ ዓርብ የምእመናን ሐዲስ መንፈሳዊ የልደት ቀን መሆኑንም በምሥጢር እንረዳለን፣ እንገነዘባለን::

(398) Raymond E. Brown et. al. eds. *Mary in the New Testament* (New York: Paulist Press, 1978), 217-218, 237-239. Malaty (Fr.), *St. Mary in the Orthodox Concept*, 47. Matero, *Refuting the Attack on Mary: A Defense of Marian Doctrines*, 37-38. Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers*, 56-57. Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 3. Galot, *Mary in the Gospel*, 210-212. Laurentin, *The Hail Mary: Its Meaning and Its Origin*, 55. Palmer, *Mary in the Documents of the Church*, 13-14. *ተአምረ ማርያም፣* ገጽ 3:: ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት፣* ገጽ 7-8::

(399) Sheen, *The World's First Love*, 30. Beima, "Hail Mary," 54. Graef, *Mary: A History of Doctrine and Devotion*, 26-27.